የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፮ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.6
ADDIS ABABA, 15th December,2025

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ፲፰

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ማሻሻያ ደንብ ……………......................................ገጽ ፲፱ሺ፬፻፲

**Content**

Regulation No. 580/2025

Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation Enforcement Regulation ....................................Page 19410

**ደንብ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ፲፰**

**የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፰፻፰/፪ሺ፮ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ፲፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**REGULATION No. 580/2025**

**REGULATION ISSUED TO AMEND THE COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ENFORCE THE PROCLAMATION FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE INFORMATION NETWORK SECURITY AGENCY**

This Regulation is issued pursuant to Article 11 Sub-Article (1) of Proclamation No. 808/2013, which re-established the Information Network Security Agency.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as “Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation Enforcement Regulation Amendment Regulation No. 580/2025”.

## ፪. ማሻሻያ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳/፪ሺ፲፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩. ከደንቡ አንቀጽ ፲፭ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተጨምሮ፣ ነባሮቹ ከአንቀጽ ፲፮ እስከ አንቀጽ ፳፫ ድረስ ያሉ ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፲፯ እስከ አንቀጽ ፳፬ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

**“፲፮/ የንግድ ድርጅት ስለማቋቋም**

፩/ አስተዳደሩ በተሰጠው ተልዕኮ መሰረት ምርት እና አገልግሎቶቹን ተደራሽ ለማድረግ እንዲያስችለው በሀገሪቱ የንግድ ሕግ መሠረት የሚሰራ ድርጅት ያቋቁማል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቋቋመው የንግድ ድርጅት፣ በአስተዳደሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሰየሙ ፭ የቦርድ አባላት ይኖሩታል፤

፫/ የንግድ ድርጅቱ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይተዳደራል፤

፬/ የድርጅቱ የአፈጻጸም ሪፖርቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል።

## 2. Amendment

The Council of Ministers Regulation No. 320/2013, the Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation Enforcement Regulation, is amended as follows;

1. The following new Article is added immediately following Article 15 of the Regulation, and the former provisions from Article 16 to Article 23 are renumbered sequentially as Article 17 to Article 24;

“**16/** Establishment of a Business Enterprise

1/ The Administration shall establish a business enterprise, in accordance with the country's commercial law, to enable its products and services accessible based on the mission entrusted to it;

2/ The business enterprise to be established pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall have 5 Board members to be appointed by the Government upon the recommendation of the Administration;

3/ The business enterprise shall be administered in accordance with the Directive issued by the Board;

4/ The performance report of the enterprise shall be submitted to the Prime Minister periodically.

**፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of December, 2025**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**